209

# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት አጭር መግለጫ

ሕ.ቤ.ቆ.ኮ

የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት
Public Relations and Information Service

የካቲት 1995

# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት አጭር መግለጫ

ሕ.ቤ.ቆ.ኮ

የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት
Public Relations and Information Service

የካቲት 1995

# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት

አገልግሎት የተዘጋጀ

የካቲት 1995

በሕዝብና ቤት ቆጠራ

መቆጠር መብትም

ግዴታም ነው!

አንድ ሰው መቆጠር

የሚገባው

አንድ ጊዜ ብቻ ነው!

## ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
| --- | --- |
| 1. መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | 1 |
| 2. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፍቺና ታሪካዊ አመጣጥ. | 8 |
| 3. የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ . . . . . | 12 |
| 4. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አመሠራረት. . | 13 |
| 5. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ዓላማዎች.. | 14 |
| 6. የኮሚሽኑ አባላት . . . . . . . . . . . . . . . | 14 |
| 7. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር . . . . . . . . . | 17 |
| 8. የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር . . . . | 19 |
| 9. የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊዎች . . . . . . . . . | 21 |
| 10. የቆጠራ ካርታ ሥራ . . . . . . . . . . . . | 21 |
| 11. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ምንነትና ጠቀሜታ. . . . . . . . | 24 |
| 12. የዜና ገጽ . . . . . . . . . . . . . . . . . . | 27 |
| 13. አባሪ የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር . . . . | |

## መግቢያ

የአንድን አገር የዕድገትና የልማት ችግሮች ለማወቅና ችግሮቹ ከታወቁ በኋላ የሚወገዱበትን መንገድ ለመቀየስ፣ እንዲቻል የሕብረተሰቡን እድገት በአግባቡ ለመምራት የሚችል አቅጣጫ ያለው ዕቅድ አስፈላጊ ነው።

ልማትና ብልጽግና ሊረጋገጥ የሚችልበትን ፕሮግራምና ፖሊሲ አዘጋጅቶ ለማውጣት፣ የዕድገት እቅድን ለማዘጋጀትና፣ እቅዱ በሥራ ላር ሲውልም ለመከታተልና ውጤቱን ለመገምገም የስታቲስቲክስ አስፈላጊነት የማያሻማ ነው።

የእቅድ መሠረትና መነሻው ነባራዊ ሁኔታ እንደመሆኑ ነባራዊ ሁኔታን የሚያመላክቱ መረጃዎችን በስታቲስቲክስ የአሰራር ስልቶችና ዘዴዎች መሰብሰብ ስለሚቻል፣ የስታቲስቲክስ የነጠላም ሆነ የድርብ ትርጉም ግንኙነት ግልጽ ሆኖ ይታያል። የእቅድን ተግባራዊነት ለመከታተል፣ ውጤቱንም ለመገምገምና ስለሁኔታው ምርምር ለማካሔድ እነዚህን የሚገልጹ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች መሰብሰብ ይኖርባቸዋል። የስታቲስቲካዊ መረጃዎች በየዘርፉ መገኘት የመንግሥትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያገለግሉ

ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ለተለያዩ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰብ ተመራማሪዎችም ጠቀሜታ አላቸው።

ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የተስተካከለና አቅምን ከግንዛቤ ያስገባ የእድገት እቅድ ለማውጣትና በሥራ ላይ ለማዋል የመረጃዎች ተሟልቶ መገኘት አስፈላጊ መሆኑን ነው። የማያዳግም፣ አስተማማኝ የልማት እርምጃዎችንና ውሣኔዎችን ለመውሰድ የስታቲስቲክስ መረጃ ጥራቱን በአስተማማኝ ሁኔታ ጠብቆ መገኘት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። የሕዝብና ቤት ቆጠራ ስታቲስቲካዊ መረጃ ጠቀሜታም ከዚሁ እውነታ የሚመነጭ ነው።

<u>የስታቲስቲክስ መረጃ እንዴት ይሰበሰባል?</u>

የስታቲስቲክስ ሥራ ልዩ ሙያና ልምድን ይጠይቃል። ይኸም ሊሆን የቻለው መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ድርጅቶች በአለባቸው ተግባርና ኃላፊነት በቋሚ መልክ የሥራ እንቅስቃሴዎችን ይዘትና ሁኔታ የሚገልፁ መዛግብት ለመያዝ ብሎም ከመዛግብት ውጭ የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ለማቀነባበርና ለመተንተን ...ወዘተ. በቅድሚያ ስታቲስቲካዊ

ዘዴዎችን፣ ሥርዓቶችንና ደንቦችን በሚገባ ማወቅ በማስፈለጉ ነው።

ስታቲስቲካዊ ዘዴዎች እንደ ስታቲስቲክሱ ሥራ ዓላማና ተግባር የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ የተለያዩ ዘዴዎች የራሳቸው የሆኑ ሥርዓቶችና ደንቦች አሏቸው። እነዚህ ሥርዓቶችና ደንቦች፣ የተተለሙ የስታቲስቲክስ ዘዴዎችን በሥራ ለመተርጎም የሚያስችሉ የአሠራር ወይም የአፈጻጸም መመሪያዎች ናቸው። የዘዴዎች ወይም የተግባር መመሪያዎች መዛባት በሚሰበሰቡት መረጃዎች ጥራት ላይ ስለሚንፀባረቅ ሁኔታዎች የሌላቸውን መልክና ገጽታ እንዲይዙ ይገደዳሉ። ስለሆነም መረጃዎች ሥርዓትንና ደንብን ሳይከተሉ ወይም ሳይንሳዊ ይዘት ሳይኖራቸው በዘፈቀደ የሚከናወኑና የሚቀናበሩ ከሆነ እነዚህን መረጃዎች መሠረት በማድረግ የሚወጣው ፓሊሲ የሚዘጋጀው ዕቅድም ሆነ አተገባበሩ ... ወዘተ. ውጤት አይኖረውም፤ ስለዚህ የስታቲስቲክስ መረጃ ሲሰበሰብ፣ ሲቀናበር፣ ሲተነተን እንዲሁም ውጤቱ ለህዝብ ይፋ ሲደረግ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግና ትክክለኛ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል። ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ የተለያዩ ዘዴዎች ቢኖሩም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. *የአስተዳደር መዛግብት መያዝ /Administrative Records/*

መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ባለባቸው ኃላፊነትና ተግባር መሠረት የሥራ እንቅስቃሴያቸውን ለማስረዳት የሚቻለው ይህንኑ የሚያመለክቱ መዛግብትን ሲይዙ ብቻ ነው። ድርጅቶች ስለሚያመርቱት ምርት ብዛትና ዓይነት፣ ሥርጭት፣ ... ወዘተ. የሚገልፁ መዛግብት መያዝ አግባብ ያለው ነው። ስለዚህ ስለመሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የሚያመለክቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማቅረብ ይህ ዘዴ ዓይነተኛና አስተማማኝ መሣሪያ ነው። ሆኖም ይህ ሥራ የድርጅቶችንና የመሥሪያ ቤቶችን የተሟላ የመዝገብ አያያዝ እወቀትንና ልምድን ይጠይቃል።

2. *የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ /Vital Statistics Registration/*

ይህ ማለት በአንድ አገር የገጠርና የከተማ የአስተዳደር ክፍሎች በሕግ የተቋቋመ የኩነቶች ምዝገባ መዋቅር ተዘርግቶ ተከታታይና ቋሚ የሆነ የልደት፣ የሞት የጋብቻና የፍቺ ኩነቶችን እንደተከሰቱ በመመዝገብ ለሕግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ መረጃ ጥንቅር የሚውሉ ግለሰባዊ መረጃዎችን

በአስተማማኝ ሁኔታ የሚመዘገብበት የስታቲስቲክስ ሥርዓት ነው። የዚህን ዓይነቱን የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ በአገራችን ለማስፋን ረዥም ጊዜና አቅምን የሚጠይቅ ቢሆንም አስፈላጊ በመሆኑ የአሠራር ሥርዓቱን ለመዘርጋት ከፍተኛ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው።

3. <u>አጠቃላይ ቆጠራ /Census/</u>

ይህ ጥናት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ጥናቱ ከሚመለከታቸው ክፍሎችና፣ ከእያንዳንዱ በነፍስ ወከፍ የተፈለጉ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያበቃ ዘዴ ነው።

ለምሣሌ ያህል:-

- <u>አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ፣</u> ስለ ሕዝብ ብዛት፣ በጾታ፣ በዕድሜና በሕዝብ ብዛት ስለደረሱ ለውጦች /ሞት፣ ልደትና ፍልሰት/፣ ስለ ትምህርት ችሎታ፣ ስለ ቋንቋ፣ ስለቤቶች ሁኔታ፣ ... ወዘተ.
- <u>አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ቆጠራ፣</u> ስለ ኢንዱስትሪ ምርት ውጤትና የሠራተኞች ሁኔታ፣ ስለ ኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ አጠቃቀም፣ ... ወዘተ.

• <u>አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ፣</u> ስለ እርሻ ውጤትና የመሬት አጠቃቀም፣ ስለቤት እንስሳት፣ በገጠሩ በግብርና ስለሚተዳደረው ሕዝብ ብዛት ... ወዘተ. ስለአጠቃላይ ቆጠራ በምሳሌነት ሊቀርቡ የሚችሉ ናቸው።

አጠቃላይ ቆጠራ በነፍስ ወከፍ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሁሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ትኩረት ስለሚያደርግ ከፍተኛ የሰው ኃይልና ወጭን የሚጠይቅ እንዲሁም መረጃዎችን ሰብስቦና አቀናብሮ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ ጊዜ የሚወስድ ሥራ ነው። ስለሆነም አጠቃላይ ቆጠራ በየጊዜያቱ የሚካሄድ ሳይሆን በየአምስት ዓመቱ ወይም በየአሥር ዓመታት ውስጥ አንድ ጊዜ የሚካሔድ የስታቲስቲክስ አሠራር ነው።

*4. የክፊል ወይም የናሙና ጥናት ማካሄድ /Sample Survey/*

አርእስቱ እንደሚያመለክተው የዚህ ዓይነቱ ጥናት፣ ጥናቱ ከሚመለከታቸው ውስጥ የተወሰኑትን በመምረጥና በማጥናት የተገኙትን መረጃዎች በመጠቀም በአጠቃላይ፣ ጥናቱ ስለሚመለከታቸው ሁሉ አስተያየት ለመስጠት ብቁ የሚያደርግ ሳይንሳዊ ዘዴ ነው። ለምሳሌ የቤተሰብን ገቢና የገቢን አጠቃቀም ሁኔታ ለማጥናት በነፍሰ ወከፍ

ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ይህን ዓይነት መረጃ ለማጠናቀር ከባድና አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ሁሉንም ቤተሰቦች ከማጥናት ይልቅ ሣይንሳዊ በሆነ ዘዴ ከጠቅላላ ቤተሰቡ ውስጥ የተወሰኑትን በመምረጥና እነሱን በጥናቱ በመሸፈን ለጠቅላላው የቤተሰብ ገቢና የገቢ አጠቃቀም ሁኔታ ግምገማ ለማድረግ የከፊል ወይም የናሙና ጥናት ዓይነተኛ ዘዴ ነው።

ጥናቱ የሚካሄደው ጥናቱ ከሚመለከታቸው የተወሰኑትን በመምረጥ ስለሆነ እንደ አጠቃላይ ጥናት/ቆጠራ ብዙ የሰው ኃይልና ወጪን ካለማስከተሉም በላይ የጥናቱን ውጤት መልክ አስይዞ ለማቅረብ ብዙ ጊዜ አይወስድም። የከፊል ናሙና ጥናት ዓይነተኛ ድክመት ለዝቅተኛ የአስተዳደር ክፍል ... ወዘተ. አስተማማኝ መረጃዎችን ለማቅረብ አለመቻሉ ነው። ለእያንዳንዱ ዝቅተኛ የአስተዳደር ክፍል መረጃ ከተፈለገ አጠቃላይ ቆጠራ ወይም መዛግብትን መጠቀም ይጠይቃል።

በአጠቃላይ ስለ ሁሉም ክፍላተ ኢኮኖሚዎች የሚያስረዳ መረጃን አሟልቶ ለመገኘት ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የስታቲስቲክስ ጥቅሞች በአስተማማኝ ሁኔታ ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎች በየዘርፉና በየጊዜያቱ የአሰባሰብ፣ የአጠናቃቀር፣

የአተናተን እንዲሁም ውጤትን ለተጠቃሚዎች የማቅረብ ሥርዓትን በሳይንሳዊ መንገድ የተከተሉ መሆን ይገባቸዋል። ሕዝብንና ቤትን የሚመለከቱ መረጃዎችም ከላይ በተጠቀሱት የስታቲስቲክስ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ይገኛሉ።

## የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፍቺ እና ታሪካዊ አመጣጥ

ዘመናዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በተሟላ መልኩ ሲገለጽ በተወሰነ ወቅትና በአገር አቀፍ ደረጃ ወይም በአገር ውስጥ በተወሰነ የአስተዳደር ክልል ስለአለው ሕዝብና ስለሚገኙት ቤቶች ብዛት፣ ስለ ሕዝቡ የዲሞግራፊ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት እንዲሁም ስለቤቶቹ ሁኔታ የሚገልጹ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀርና ከዚያም አስተማማኝነቱንና ትክክለኛነቱን በመገምገም የተገኘውን ውጤት ለተጠቃሚዎች የማሰራጨት ተግባራትን ያጠቃልላል። የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት ከአነስተኛ የአስተዳደር ክልል ማለትም ከገበሬ ማህበር ወይም ከቀበሌ ማህበር ጀምሮ እስከ ብሔራዊ ክልል ከዚያም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሕዝብ ነክ መረጃዎችን ያስገኛል።

ሕዝብ ቆጠራ በአለም ውስጥ መቼ እንደተጀመረ ጊዜው በትክክል ባይታወቅም ከክርስቶስ ልደት በፊት ቆጠራ ያካሄዱ አገሮች እንደነበሩ ይታወቃል። ለምሳሌ ያህል፡-

- በባቢሎን በ3800 ከክርሰቶስ ልደት በፊት
- በቻይና በ3600 ከክርሰቶስ ልደት በፊት
- በግብጽ በ2500 ከክርሰቶስ ልደት በፊት የሕዝብ ቆጠራዎች እንደተካሄዱ የጽሁፍ ማስረጃዎች ያመለክታሉ።

ጥንታዊ ግሪክና ሮም በተደጋጋሚ ብዙ የሕዝብ ቆጠራዎች እንዳካሄዱ ይነገራል። የጥንቱ የሕዝብ ቆጠራ ዋና ዋና አላማዎች፣ ግብር ለመሰብሰብ፣ ለውትድርና ምልመላ፣ እንዲሁም የሥራ ግዳጆችን ለማሟላት የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ለመሰብሰብ ነበር። በሚካሄዱት የሕዝብ ቆጠራዎች ሲሰበሰቡ የነበሩት መረጃዎችም ሁልጊዜ የሚዛመዱት ከቤተሰብ ኃላፊ፣ ከግብር ከፋይ ወይም ለውትድርና ምልመላ እንዲያመች ከጎልማሳ ነዋሪዎች ጋር ብቻ ነበር። በ14ኛውና በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአንዳንድ የአውሮፓ ሀገሮች ስለመሳፍንቱና ስለቀሳውስቱ ብዛት በመዝገብ ላይ ይሰፍር ነበር።

የሁሉንም ኗሪዎች ሕዝብ ነክ መረጃዎች በመሰብሰብ የቀዳሚነቱን ሥፍራ የያዘችው ስዊድን ናት። በ17ኛው

ክፍለ ዘመን በስዊድን ቤተክርስቲያናት በቤተክህነት አስተዳደር ክልል ስለሚኖሩት ሰዎች ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው የወሊድ፣ የሞትና የጋብቻ ክስተቶችን እንዲመዘግቡ በህግ ታውጆ ነበር። ይህ እስካሁንም በኖርዌይ፣ በስዊድን፣ በዴንማርክ፣ በፊንላንድ በኔዘርላንድስ እና በቤልጅግ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ /Vital Statistics Registrations/ በመባል እየተሰራበት ነው። ይሁን እንጂ ይህም ቢሆን የተሟላ የአጠቃላይ የሕዝብ ቆጠራ ባህርይ አልነበረውም።

ቀስ በቀስ ወታደሮችን ለመመልመልና ግብር ለማስከፈል ሲባል በ17ኛው ክፍለ ዘመን ይከናወን የነበረው የሕዝብ ቆጠራ ሥራ የአላማ ለውጥ በማድረግ ሌሎች የሕዝቡን የማህበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱ አርእስቶችን በመጨመር ይካሄድ ጀመር። ለምሳሌ ስለአስተዳደር፣ ስለንግድ ሥራ፣ ስለትምህርት፣ ለምርምር ስለሚጠቅሙ መረጃዎች፣ ... ወዘተ.

ከዚህ አንፃር የመጀመሪያው ትክክለኛና ዘመናዊ ቆጠራ የተካሔደው እ.ኤ.አ በ1665 በካናዳ ሲሆን በወቅቱ "የኒው ፍራንስ" ገዢ ጃን ታሎን ኩቤክ ከተቋቋመችበት ከ1608 ጀምሮ የሕዝቧ ብዛት ምን ያህል እንደጨመረ የማወቅ ፍላጎት ስላደረባቸው ቆጠራ እንዲካሔድ አዘዙ።

በዚሁም መሠረት የቆጠራው ጥያቄዎች የእያንዳንዱን ሰው ስም፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ የጋብቻ ሁኔታ እና የሥራ ሁኔታን ያካተተ እንዲሆን ተደረገ። በተመሳሳይ ሁኔታ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ በ1790፣ በእንግሊዝና በፈረንሳይ በ1801፣ በሩሲያ በ1897 እ.ኤ.አ. ዘመናዊ ቆጠራዎች ተካሔደዋል።

ወደ አህጉራችን ስንመለስ በአሥራ ዘጠነኛው ምእተ አመት አጋማሽ አካባቢ ሕዝብ ቆጠራዎች እንደተካሔዱ መረጃዎች አሉ። ለአብነት ያህል በናይጀሪያ (ሌጎስ አካባቢ) እ.ኤ.አ. በ1886፣ በጋና እ.ኤ.አ. በ1891 ቆጠራዎች ተካሔደዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ቀደምት ቆጠራዎች ከቀኝ ገዢ አገሮች የህዝብ ቆጠራዎች ጋር የተቆራኙ ነበሩ። ማለትም ቅኝ ገዥ አገሮች በአገራቸው ቆጠራ ሲያካሂዱ ቅኝ በሚገዟቸው አገሮችም የሕዝብ ቆጠራ ያካሔዱ ስለ ነበር ነው።

የሕዝብ ቆጠራ ሒደት ቤቶችንም እንዲያካትት የተደረገው እ.ኤ.አ. በ1940 በአሜሪካ ሲሆን ቤቶችን የሚመለከቱ ዝርዝር ጥያቄዎች በቆጠራ እስኪካተቱ ሌላ አርባ ዓመት ወስዷል። እ.ኤ.አ. እስከ 1984 ዓ.ም ድረስ በዓለም ላይ ራሳቸውን የቻሉ አገሮች ሆነው ነገር ግን አጠቃላይ ዘመናዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች አንዴም

ያላካሄዱ አገሮች ሶስት ነበሩ። ቻድ፣ ዛየርና አገራችን ኢትዮጵያ።

## የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ በተወሰኑ አካባቢዎች ማለትም በአዲስ አበባ በ1953 እና በ1961 የሕዝብ ቆጠራ የተካሄደ ሲሆን ተመሳሳይ ቆጠራዎችም በሌሎች ጥቂት ትላልቅ ከተሞች ተካሂደዋል። ዘመናዊ የሕዝብ ቆጠራ መስፈርትን ያሟላ ቆጠራ እንዲካሔድ ለጠቅላይ ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ለዛሬው የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 303/1964 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በ1968 ለማካሔድ ታቅዶ ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በወቅቱ ያገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ማለትም በነበረው የመንግሥት ለውጥ ምክንያት ሁኔታዎች ባለመፍቀዳቸው ቆጠራው ሊካሄድ አልቻለም። በመሆኑም በኢትዮጵያ የመጀመሪያውና ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ያሟላ አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደው በግንቦት ወር 1976 ዓ.ም ነበር። በተመሣሣይ ሁኔታ ቀጣዩና ሁለተኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በጥቅምት ወር 1987 ዓ.ም ተካሒዷል። በአሁኑ ወቅትም የሕዝብና ቤት ቆጠራ

ኮሚሽን ጽ/ቤት በአዋጅ ተቋቁሞ በ1997 ዓ.ም የሚካሔደውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ለመጀመር ቀዳሚ ተግባር የሆነውን የቆጠራ ካርታ ሥራ የአሰልጣኞች ስልጠና በማካሄድ ላይ ይገኛል።

## የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አመሠራረት

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 103 መሠረት በአዋጅ የተቋቋመ መንግሥታዊ ተቋም ነው። በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 180/1991 ዓ.ም በግልጽ እንደተቀመጠው፣

- *የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ለሚደረገው ሕገ-መንግሥታዊ አደረጃጀትና ለፖለቲካዊ ሥርዓት ዝግጅት አስፈላጊ ስለሆነ፡-*
- *ትክክለኛውን የሕዝብ ብዛት ማወቅ በሀገር አቀፍ ወይም በተወሰነ ክልል አስተዳደር እርከን ደረጃ ለሚደረጉ ምርጫዎች አፈፃፀም መሠረት በመሆኑ፣ የተግባሩን አስፈላጊነት፣ ስፋትና ውስብስብነት በማገናዘብ ኮሚሽኑ እንዲቋቋም ተደርጓል።*

## የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ዓላማዎች

ከላይ በተጠቀሰው የአዋጅ ቁጥር *መሠረት፣* ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

*1ኛ. ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች እና ለምርጫ ዕቅድ ዝግጅት አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ፣ እንዲሁም ለምርምር የሚጠቅሙ ሕዝብና ቤትን የሚመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መገምገምና ማሰራጨት፣*

*2ኛ. የሕዝብና የቤቶች ምዝገባ በመላ ሀገሪቱ እንዲሠራበት መሠረታዊ ጥናቶችን በማካሄድ የሚደራጁበትን መንገድ መቀየስ፣*

### የኮሚሽኑ አባላት

በማቋቋሚያ አዋጁ እንደተገለጸው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አባላት በሕገ *መንግስቱ* አንቀጽ 103 ንዑስ አንቀጽ(2) በተደነገገው *መሠረት* በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በምክር ቤቱ የተሾሙ ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢም ከአባላቱ *መካከል* በምክር ቤቱ ተለይቶ ተሰይሟል።

የኮሚሽኑ አባላትን ስብጥር በሚ*መ*ለከት ከዘጠኝ ክልሎች፣ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ከፌዴሬሽን ምክር ቤትና ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን *መሥሪያ* ቤት

የተውጣጡ መሆኑ፣ ኮሚሽኑ ወደፊት እንዲያከናውን የተጣለበትን ሀገራዊ የኃላፊነት ስፋት በብቃት ለመወጣት የሚያስችለውን ፅኑ መሠረት የሚጥል እንደሆነ ይታመናል።

ቀጥሎ የቀረበው የኮሚሽኑ አባላት የስም ዝርዝርና በኮሚሽኑ ያላቸው ኃላፊነት ድርሻ ነው፡-

1. ዶ/ር አብዱላሂ ሐሰን
   የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
   ዋና ሥራ አስኪያጅ
   ሰብሳቢ
   <u>አዲስ አበባ</u>

2. የተከበሩ ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ
   የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈጉባኤ
   አባል
   <u>አዲስ አበባ</u>

3. የተከበሩ አቶ አሰፋ ብሩ
   የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ኃላፊ
   አባል
   <u>አዲስ አበባ</u>

4. የተከበሩ አቶ መለሰ ማሪሞ
   የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር
   አባል
   <u>አዋሳ</u>

5. የተከበሩ ዶ/ር መሐመድ አልይ
   የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር
   አባል
   <u>ፊንፊኔ</u>

6. የተከበሩ አቶ አባዲ ዘሞ
   የትግራይ ብ/ክ/መንግሥት
   የአቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ
   አባል
   <u>መቀሌ</u>

7. የተከበሩ አቶ ታደሰ ካሳ
   የአማራ ብ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር
   አባል
   <u>ባህር ዳር</u>

8. የተከበሩ አቶ አብዱልአዚዝ መሐመድ
   የሐረሪ ሕዝብ ብ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር
   አባል
   <u>ሐረር</u>

9. የተከበሩ አቶ ሐመዱ አሊ
   የአፋር ብ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር
   አባል
   <u>አሳይታ</u>

10. የተከበሩ አቶ አብዲ ጅብሪል
    የሶማሌ ብ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር
    አባል
    <u>ጂጂጋ</u>

11. የተከበሩ አቶ ኤፍሬም በዳሳ
    የጋምቤላ ሕዝብ ብ/ክ/መንግሥት ም/ቤት ጸሐፊ
    አባል
    <u>ጋምቤላ</u>

12. የተከበሩ አቶ ረሽድ መሐመድ
የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መንግሥት
ም/ርዕሰ መስተዳድር
አባል
አሶሳ

13. አቶ አማረ ኢሳይያስ
የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ተ/ዋና ጸሐፊ
አባልና የኮሚሽኑ ጸሐፊ
አዲስ አበባ

## የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር እንደሚከተለው ተዘርዝሯል

- በየአስር ዓመቱ አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ እንዲከናወን ማድረግ፣
- የቆጠራ ካርታ ሥራ እና የሕዝብ ቆጠራን በሚመለከት የፖሊሲ መመሪያ ማውጣት እና አፈፃፀማቸውን መከታተል፣
- የሕዝብ ብዛት በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ እንዲሁም በገጠር ቀበሌዎች ተለይቶ በፆታ፣ በዕድሜ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣

- ስለቆጠራ ካርታ ሥራ እንዲሁም ስለቆጠራ ምንነት ለሕዝቡ ማሳወቅ፣
- በሚያወጣው ደንብ መሠረት በክልል፣ በወረዳና አስፈላጊ ሆነው በሚያገኛቸው ተጨማሪ የአስተዳደር እርከኖች ደረጃ ሌሎች ኮሚሽኖችን በቆጠራ ማካሄጃ ወቅት ማቋቋም፣ እንዲሁም ስልጣንና ተግባራቸውን የአባላቱን አሰያየምና የስብሰባ ሥነስርዓታቸውን መወሰን፣
- ከፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚቀርበው የብሔረሰቦች ዝርዝር መሠረት እና በሕዝብና ቤት ቆጠራ አማካኝነት የብሔረሰቦችን ብዛትና ስርጭት እንዲገኝ ማድረግ፣
- የሕዝብ ቁጥር እድገትን ለመተንበይ የሚያስችሉ የናሙና ጥናቶች እንዲከናወኑ ማድረግ፣
- በየክልሉ በሚገኙ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ከተሞች እና የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ያሉት ብሔረሰቦች ብዛት በፆታና በዕድሜ ተከፋፍሎ በገጠርና በከተማ ተለይቶ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣
- በዚህ አዋጅ መሠረት በሚካሄደው የቆጠራ አፈፃፀም ሂደት በስፋቱና በዓይነቱ የቆጠራውን ውጤት ሊያዛባ የሚችል ግድፈት ስለመከሰቱ በቂ መረጃ ካገኘ ለምክር ቤቱ በማሳወቅ ውጤቱን መሠረዝ፣ እንደገና ቆጠራ እንዲካሄድ ማዘዝ፣

♦ የቆጠራ ውጤቶችን ማረጋገጥ፣ ለምክር ቤቱ ማቅረብ፣ እንዲሁም ለሕዝብ በይፋ እንዲገለጽና በተለያዩ መንገዶች እንዲሰራጭ ማድረግ፣

♦ የጽህፈት ቤቱን በጀት ለምክር ቤቱ አቅርቦ ማስፈቀድና በትክክል በሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣

♦ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችንና መሠረተ ሀሳቦችን በመከተል የጽህፈት ቤቱን ሙያተኞች ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል፣ የቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ ማውጣት፣

♦ ስለሥራ አፈፃፀሙ በየጊዜው ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣

## የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች አሉት፡-

* የቆጠራ ሥራ የማከናወን፣
* የቆጠራና የናሙና ጥናት ዕቅድ አዘጋጅቶ ለኮሚሽኑ የማቅረብ፣
* ቆጠራ እና የናሙና ጥናት ሥራ የማካሔድ፣ ለዚሁም አፈፃፀም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፤ (፭) መሠረት የሚቋቋሙትን ሌሎች ኮሚሽኖች እንቅስቃሴ የመምራት፣

የማስተባበርና የመቆጣጠር፣

* ለቆጠራ እና ለናሙና ጥናት አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መጠይቆች፣ መመሪያዎችና ልዩ ልዩ ቅጾች እንዲሁም ቁሳቁሶች የማዘጋጀትና የማሰራጨት፣
* ሕዝብና ቤትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አግባብ ያላቸውን ሰነዶችና መዛግብት የመመርመር፣ ምርመራውንም ለማከናወን ተገቢ በሆነ ጊዜ ወደ ማንኛውም ሰው ቤት ወይም ቅጥር ግቢ የመግባት፣
* ለቆጠራ እና ለናሙና ጥናት አፈፃፀም የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል የማሰልጠን፣
* በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፯) መሠረት የቆጠራ ካርታ ሥራ ወይም ቆጠራ ለማካሔድ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኞች፣ ንብረትና አገልግሎት የመጠቀም፣
* የተሰበሰበውን የቆጠራ መረጃ ማደራጀት፣ መተንተንና ሪፖርቱን አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለኮሚሽኑ የማቅረብ፣
* በየጊዜው የሚደረገውን የቆጠራ አፈፃፀም የመገምገም እንደ አስፈላጊነቱም የአሠራር ማሻሻያ ጥናቶች እንዲካሄዱ የማድረግ፣
* የንብረት ባለቤት የመሆን፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፣

★ በኮሚሽኑ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ሌሎች አግባብ ያላቸውን ተግባሮች የማከናወን።

## የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊዎች

- ኮሚሽኑ በዋና ጸሐፊ እና በምክትል ዋና ጸሐፊ የሚመራ ጽህፈት ቤት በአዲስ አበባ አቋቁሟል።
- ዋና ጸሐፊው በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማል፣
- ምክትል ዋና ጸሐፊው በኮሚሽኑ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ይሆናል፣

## የቆጠራ ካርታ ሥራ

የሕዝብና ቤት ቆጠራ እጅግ አድካሚና ጥንቃቄን የሚጠይቅ ውስብስብ ተግባር ነው። በዚህም ምክንያት ከፍተኛ ቅድመ-ዝግጅት የጊዜ፣ የበጀት፣ እቅድና በሥራው ላይ የሚሰማራ በርካታ የሰለጠነ የሰው ኃይል የሚጠይቅ ሲሆን የቆጠራ ካርታ ሥራ የዚህ ግዙፍ ተግባር አንዱና ዋነኛው ነው።

የቆጠራ ካርታ ማለት በሕዝብ ቆጠራ ክንውን ወቅት ሰው ሳይቆጠር እንዳይቀር ለማድረግ የቆጠራው ክንዋኔ ከመጀመሩ በፊት የቆጠራ ቦታና የመቆጣጠሪያ ሥፍራ

ካርታዎችን ማዘጋጀት ማለት ነው። በአሁኑ ወቅት እየተከናወነ ያለው የቆጠራ ካርታ ሥራ ዝግጅት በ1997ዓ.ም ለሚካሄደው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ሲሆን በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ሥራው ለ21 ወራት እንደሚቆይ ተገምቷል። በዚህ የቆጠራ ሥራ ላይ 130 ቡድን የሚሰማራ ሲሆን በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ 1 ተቆጣጣሪ፣ 6 የካርታ ሠራተኛ፣ 1 ሾፌርና 1 ካምፕ ጠባቂ ይኖራሉ። ከዚህም በላይ ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ቡድኖችን የሚያስተባብር አንድ አስተባባሪ ይመደባል።

የቆጠራ ካርታ ሥራ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የሽፋን ቁጥጥር ለማድረግ፡-

የቆጠራና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎች በቆጠራ ወቅት የቤተሰቦችንና የቤቶችን መዘለል ወይም ተደጋግሞ መቆጠር ለመከላከልና ለመቆጣጠር ያስችላሉ።

ለ. የጥራት ቁጥጥር ለማድረግ፡-

የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎች በቆጠራ ወቅት የቁጥጥር ተግባርን ለማቀናጀት የመስክ ሥራ ክንውን በተገቢው መንገድ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ያስችላሉ።

ሐ. የሰውኃይል ብዛትን ለመወሰን፡-

የቆጠራ ቦታዎችና የመቆጣጠሪያ ቦታዎች መመሥረትና ካርታዎችን ማዘጋጀት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ለቆጠራው ሥራ ምን ያህል ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች እንደሚያስፈልጉት በቅድሚያ ለማወቅ ይረዳዋል። በዚህ ዓይነት በቆጠራው ሥራ ወቅት የሰው ኃይል እጥረት እንዳይከሰት ተገቢው ቅድመ ዝግጅት ሊከናወን ይችላል።

መ. ለመስክ ሥራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን (ሎጀስቲክስ) ለመወሰን፡-

የቆጠራው ካርታ ሥራ ውጤት ለቆጠራው የሚያስፈልገውን የቆጠራው መጠይቆች ብዛት፣ የጽሕፈት መሣሪያዎች፣ የቅጾችና መጠይቆች ብዛት፣ የጽሕፈት መሣሪያዎች፣ የተሽከርካሪዎች፣ ...ወዘተ ብዛት በቅድሚያ ለማወቅ ይረዳል።

ሠ. ተመጣጣኝ የሥራ ክፍፍል (Fair distribution of workload) ለመፍጠር፡-

ሐገሪቱን በቆጠራና በመቆጣጠሪያ ቦታዎች መከፋፈል በቆጠራ ወቅት እያንዳንዱ ቆጣሪና ተቆጣጣሪ የተመጣጠነ የሥራ ድርሻ እንዲኖረው ለማድረግ ይረዳል። ይህም ሁሉም የቆጠራ ሠራተኞች ሥራቸውን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለመፈጸም ያስችላቸዋል።

ረ. ስታቲስቲካዊ ናሙና ፍሬም ዝግጅት ለማድረግ፡-

ሐገሪቱን በቆጠራ ቦታዎች መከፋፈል በየጊዜው ለሚካሄዱ የሥነ-ህዝብ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥናቶች ፍሬም ለማዘጋጀት ይረዳል።

## የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ምንነትና ጠቀሜታ

የሰው ልጆች ማህበረሰባዊ አኗኗር ዓይነትና ይዘት እየሰፋ በሄደ መጠን አስተዳደራዊ አቋሙ ከልማዳዊው አሠራር ቀስ በቀስ እየተላቀቀ በሕግና በሥርዓት ወደ ተደገፈ ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር ማደጉ በሕብረተሰብ ታሪክ የታየ የእድገት ውጤት ነው። የዘመናዊ መንግሥት አስተዳደር ሥርዓት አፈጣጠሩ በግለሰባዊና በቡድናዊ ግንኙነቶች ተራክቦ ሂደት እንደመሆኑ የእነዚህን ግንኙነቶች በጊዜ፣ በቦታና በሁኔታዎች የመለዋወጥና የመወሳሰብ ባህርይ ለመቆጣጠር እንዲቻል በህጋዊ የጽሑፍ መረጃ ድጋፍ የመስጠትና መረጃውንም የማደራጀት ስልት እያደገ መጣ።

በዚህም የወሳኝ ኩነቶች ማለትም፣ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ አፈፃፀም ሥርዓት ማህበረሰባዊ ተቀባይነትና ህጋዊ ድጋፍ አገኘ።

በአንድ ሀገር አግባባዊና ህጋዊ የአስተዳደር ስርዓትን ለማስፈን ዜጎችን በቀጥታና በማህበራዊ ተቋማት አማካኝነት ከመንግሥት ጋር ለማገናኘት የሚያስችላቸውን ህጋዊ የመረጃ ፍሰት ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። ይህን አሠራር እውን

ለማድረግም ሁለት የመረጃ ግብአቶች ያስፈልጋሉ። እነርሱም ህጋዊ የወሳኝ ኩነቶች መረጃዎችና ጥቅል የወሳኝ ኩነቶች መረጃዎች ናቸው። እነዚህ መረጃዎች የዜጎች ሰብአዊ መብቶች መከበራቸውንና አስተዳደራዊ ጉዳዮች በወቅቱ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያበቁ ሲሆን ደረጃ በደረጃም የመንግሥትን አስተዳደር ወደ ዘመናዊ የህዝብ አስተዳደር ለማሸጋገር ፅኑ መሠረት ይሆናሉ።

ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ሁለት አበይትና ጠቃሚ የመረጃ ውጤቶች ይገኛሉ። እነዚህም ግለሰባዊ የሕግ መረጃዎችና ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ናቸው። ግለሰባዊ መረጃዎች ለሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች በግብዓትነት የሚያገለግሉ ሲሆን እነርሱም፡-
ለሕግ አፈፃፀም ስርአት፣ ለአስተዳደር ማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ፣ እና የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃን ለማጠናቀር ናቸው። እስከ ዛሬ ድረስ በሀገራችን እነዚህ የስነ-ሕዝብ መረጃዎች ባለመኖራቸው የተጠቀሱትን የመረጃ አገልግሎቶች ለማግኘት ሳይቻል ቆይቷል። ስለሆነም የእነዚህ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት መቋቋም ለህግ፣ ለአስተዳደርና ስታቲስቲክስ ጥንቅር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት መቋቋም የሚከተሉትን ዋና ዋና የቫይታል ስታትስቲክስ መረጃዎችን ያስገኛል።

- ዓመታዊ የልደት መጠንን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ለማስገኘት፣
- የየዓመቱን የሞት መጠን ማለትም የህፃናትን፣ የወጣቶችንም ሆነ የአዋቂዎችን በተለያየ መረጃ በማስደገፍ እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ለማስገኘት።
- ለሞት መንስኤ የሆኑ ምክንያቶችን እስከ ዝቀተኛው የአስተዳደር አካል ድረስ ለማወቅ፣
- የየዓመቱን የጋብቻና የፍቺ መጠን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ድረስ ለማስገኘት፣
- ከዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ጀምሮ በተፈጥሮ ክስተቶች (በልደትና ሞት) ምክንያት የሚጨመረውንና የሚቀነሰውን የህዝብ ቁጥር በየዓመቱም ሆነ በአመት ባነሰ ጊዜ እስከ ቀበሌ የአስተዳደር እርከን ለማስላት የሚያስችል መረጃ ለማስገኘት፣
- የየዓመቱን የህዝብ ብዛት መረጃ እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ለማወቅ።

## የዜና ገጽ

☞ በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት አዲስ ለተመደቡ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስለ አዲሱ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ አዋጅና ስለ ሥራ አፈፃፀም ምዘና ሥልጠና ተሰጠ።

ከታህሳስ 15-18/95 በቆየው በዚህ ስልጠና ላይ ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ የተመደቡ ባለሙያዎች ስለ ሥራ ዕቅድና ስለሥራ አፈፃፀም መለኪያ ተገቢውን ገለፃና ማብራሪያ ያደረጉ ሲሆን ሰልጣኞቹም በግልጽነት ላይ የተመሰረተ ውይይትና የቡድን ሥራ ልምምድ አድርገዋል።

x x x x x x

☞ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣንና የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽህፈት ቤት ሠራተኞችና የማኔጅመንት አባላት በጋራ ባካሄዱት ስብሰባ በተከሰተው የድርቅ አደጋ ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች መርጃ የሚውል ከደመወዛቸው አስር በመቶ ተቀንሶ እንዲሰጥላቸው ተስማምተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ የመሥሪያ ቤቶቹ የመረዳጃ ዕድር አባላት ከተቀማጭ ገንዘብ አራት ሺ. ብር ወጪ ሆኖ እንዲሰጥላቸው ከመወሰቸውም በላይ የደንብ ልብስ የሚገባቸው ሃያ ሁለት ሠራተኞች በዓመት ሁለት ጊዜ

ከሚሰጣቸው ውስጥ የአንደኛው የደንብ ልብስ ማሰፊያ ገንዘብ ለዕርዳታው እንዲውል ፈቅደዋል።

X X X X X

☞ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ለቀጣዩ አገር አቀፍ ቆጠራ የሚያገለግል የካርታ ሥራ እንደሚጀመር አስታወቀ።

ይህ የተገለጸው በ13/5/95 ዓ.ም በመ/ቤቱ አዳራሽ በተደረገ አጠቃላይ የሠራተኞች ስብሰባ ሲሆን፣ በዕለቱ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ዋና ፀሐፊ አቶ አማረ ኢሳይያስ የካርታ ስራው በቅርቡ እንደሚጀምር አስታውቀው እያንዳንዱ ሠራተኛም የግልና የጋራ ኃላፊነቱን በብቃት እንዲወጣ ከአደራ ጋር አሳስበዋል።

በስብሰባው ላይ በአሠራር ስለሚያጋጥሙ ችግሮችና መፍትሂዎቻቸው ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን ከሠራተኞቹ ለቀረቡ ጥያቄዎችም መልስ ተሰጥቷል።

X X X X X X

☞ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በ1997 ዓ.ም ለሚያካሂደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት አካል

የሆነው የቆጠራ ካርታ ሥራ የአሰልጣኞች ስልጠና የካቲት 17/95 ዓ.ም ጀምሯል።

በወረዳ 2 ቀበሌ 17 ውስጥ በሚገኘው የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የከተማ ልማት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ውስጥ የተጀመረውን ይህን ስልጠና በንግግር የከፈቱት አቶ አማረ ኢሳይያስ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ዋና ፀሐፊ ናቸው።

በዚህ ስልጠና ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣንና ከክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ እንዲሁም ከሕ.ቤ.ቆ.ኮ. ጽ/ቤት የተውጣጡ 97 ያህል የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሳታፊዎች የተገኙ ሲሆን ከነዚሁ ሰልጣኞች መካከል 4ቱ ሴቶች ናቸው።

ይህ የአሰልጣኞች ስልጠና በ1997 ዓ.ም ለሚካሂደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዝግጅት አንዱና አብይ ሥራ መሆኑን ዋና ጸሐፊው ገልፀው ሰልጣኞቹ በቆይታቸው ወቅት በንቃት በመሳተፍ የተጣለባቸውን ኃላፊነት እንደሚወጡ ያላቸውን እምነት ገልፀዋል።

x x x x x


የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን በሕገ መንግሥቱ ከተቋቋመ ወዲህ የመጀመሪያ የሆነው የአባላት አንደኛ መደበኛ ስብሰባ መጋቢት 08/95 በጊዮን ሆቴል ይካሔዳል።

ከሁሉም የክልል መንግሥታት፣ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ከፌዴሬሽን ም/ቤትና ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ የተወከሉ አባላትን የያዘው ይህ የኮሚሽኑ ስበሰባ በተለያዩ አጀንዳዎችና ከሕዝበና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በሚቀርብለት የ6 ወር የእንቅስቃሴ ሪፖርት ይነጋገራል።

ከዚህም በላይ ስብሰባው የመጭውንና በ1997 ዓ.ም የሚካሔደውን ሦስተኛውን ዙር የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዝግጅት በመመርመር ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን የጽ/ቤቱን የ1996 ዓ.ም የካፒታል በጀትም እንደሚያጸድቅ ይጠበቃል።

X X X X X X X X X

# አባሪ የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር



## የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

የካቲት 1995 ዓ.ም

### ዓላማ

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. ለአስተዳደራዊ ጉዳዮችና ለምርጫዎች ዕቅድ ዝግጅት፣ ለዕቅድ አፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ለምርምር የሚጠቅሙ ሕዝብና ቤትን የሚመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናከር፣ መገምገምና ማሰራጨት፣

2. የሕዝብና ቤቶች ምዝገባ በመላ ሀገሪቱ እንዲቋቋምና እንዲሰራበት መሰረታዊ ጥናቶችን በማካሄድ የሚደራጁበትን መንገድ መቀየስ።

☎ 124538
Fax 251-1-563885
E.mail – popcen@telecom-net.et

✉ 59047
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa Ethiopia

የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት